## המשך פעילויות בעקבות הסיפור - ?እንደዚህ ያለ ነገር የት ሰማህ

በ: አን ካራሂ
ምሳሌዎች: አን ካራሂ
הוֹצָאָה: מטר
የእድሜ ክልል: ሁለተኛ ክፍል




שִׂיחָה

**እንደሆነ ሠምቻለሁ ...**

ወሬ" ስለሚለው ቃል ትርጉም መወያየት ይችላሉ፡- ከሌሎች በሰማናቸው ነገሮችና በምናውቃቸው ነገሮች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ያጋጠመዎትን ወሬ አጋጣሚዎችን ማጋራት ይችላሉ። ምን ምላሽ ሰጡ? ምን ተሰማዎ? ?አስችሎዎትስ ዝም ብለው በጭራሽ ሳይናገሩ ቀሩ? ሌላ ወሬ ሲያጋጥምዎ ምን ያደርጋሉ

שִׂיחָה

**ቤተሰባዊ የሻይ ሠዓት**

ልክ እንደ ድብና ድንቢጧ እርስዎም ቀኑን ሙሉ በቤተሰብ አባላት ላይ የተፈጸሙ ታሪኮችንና ልምዶችን የምታካፍሉበት የቤተሰብ ሻይ ጊዜ ሊያሳልፉ ይችላሉ። የድብ ምክርን ተጠቅመው እውነተኛ፣ አስደሳችና ጠቃሚ ተሞክሮዎችንና ታሪኮችን ማካፈል ይችላሉ።

מִשְׂחָק

**የተቋረጠ ግንኙነት -- በዱር እንስሳት አንድምታ**

በአንድ ሰው ጆሮ ውስጥ አንድ ዓረፍተ ነገር በሹክሹክታ የሚናገሩበትን ተወዳጅ ጨዋታ ታውቃላችሁ? አሁን የእንቆቅልሹን ዓይነት ይሞክሩት – በእያንዳንዱ ጊዜ የመጀመሪያው ተሣታፊ አንዱን የጫካ እንስሳት የሚገልጽ አንድ ዓረፍተ ነገር በሹክሹክታ ሲናገር ለምሣሌ:- ዛፎችን እወጣለሁና ፍሬዎችን እሰነጥቃለሁ። የመጨረሻው ተሣታፊ የትኛው እንስሳ እንደሆነ መገመት ይኖርበታል።

קְרִיאָה

**ከቃላት በላይ**

ሥዕሎቹ በተደጋጋሚ ንባቦች ላይ ሊያስተውሏቸው የሚችሏቸው ትናንሽና አስደሳች ዝርዝሮችን ይይዛሉ። ከድንቢጥ በስተቀር የትኞቹ እንስሳት በእያንዳንዱ ገጽ ላይ እንደሚታዩ መፈለግ ይችላሉ። በመስኮቱ አጮልቀው የሚወጡት እንስሳት እዚያ ምን እያደረጉ ነው ብለው ያስባሉ? በመጨረሻው ገጽ ላይ ያለ ቃላት የቀረበ ምሣሌ አለ። ድብ ለእንስሳቱ የሚናገረውን ታሪክ ለመገመት ይሞክሩ ።

סִרְטוֹנִים

**QR ኮድ**

ኮዱን ስካን በማድረግ ማንበብና መጻፍን ቀደም ብለው ከተማሩ ልጆች ጋር የማንበብ ዋጋን በተመለከተ ልዩ ቪዲዮ ይመልከቱ።

הַשְׁרָאָה

**ፒንተረስት**

[ተጨማሪ ስራዎችን፣ ግጥሞችንና እንቅስቃሴዎችን በፒጃማ ቤተ መጻህፍት ፒንተረስት ላይ]

עוד פעילויות באתר ספריית פיג'מה www.pjisrael.org